የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፱
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፩ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 49
ADDIS ABABA - 6th September, 2000

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች
ምክር ቤት ደንብ ........................................ ገጽ ፩ሺ፫፻፺፪

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 67/2000
Emergency Food Security Reserve Administration Establishment Council of Ministers Regulations .......................................... Page 1392

## የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደርን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፮ (፫) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፡

፩· "ኮሚሽን" ወይም "ኮሚሽነር" ማለት እንደአግባቡ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር ነው፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO ESTABLISH AN EMERGENCY FOOD SECURITY RESERVE ADMINISTRATION

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 6 (3) of the Disaster Prevention and Preparedness Commission Establishment Proclamation No. 10/1995.

### PART ONE
### *General*

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Emergency Food Security Reserve Administration Establishment Council of Ministers Regulations No. 67/2000."

2. *Definitions*

In these Regulations:

1) "Commission" or "Commissioner" means Disaster Prevention and Preparedness Commission or Disaster Prevention and Preparedness Commissioner, respectively;

፮· **የክምችቱ ባለቤት**

በክምችቱ ላይ የባለቤትነት መብት የሚኖረው የፌዴራሉ መንግሥት ይሆናል።

## ክፍል ሦስት

## የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደርን ስለማቋቋም

፯· **መቋቋም**

፩· የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር /ከዚህ በኋላ "አስተዳደሩ" እየተባለ የሚጠራ/በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪· የአስተዳደሩ ተጠሪነት ለኮሚሽኑ ይሆናል።

፰· **ዋና መሥሪያ ቤት**

የአስተዳደሩ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ለክምችት አያያዝ አመቺ በሆኑ ስትራቴጂክ ቦታዎች የማከማቻ መጋዘኖችንና ቅርንጫፍ የመጋዘን አስተዳደር ጽ/ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል።

፱· **የአስተዳደሩ ሥልጣንና ተግባር**

አስተዳደሩ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

፩· ክምችቱን የማስተዳደር፣

፪· ለክምችት አስፈላጊ የሆነውን ምግብና ምግብ–ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን በእርዳታ የማግኘትና የመቀበል፣ እንዳስፈላጊነቱም ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ ሀገር የመግዛት፣

፫· በእርዳታ ወይም በግዥ ምግብና ምግብ–ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን የማከማቸት፣

፬· አስቸኳይ የምግብ እጥረትን ለመቋቋም ይቻል ዘንድ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከክምችቱ ምግብ በብድር እንዲወጣ የማድረግ፣

፭· የምግብ ክምችቱን ከተባይ ጥቃት ለመከላከል የሚያስፈልጉ ፀረ–ተባይ ኬሚካሎችንና መድሃኒቶችን የመያዝ፣ በክምችት የቆየ እህልን የማለዋወጥ፣ የምግብ ክምችቱ ላይ የጥራት ቁጥጥር ለማድረግ የሚረዳ ላቦራቶሪ የማደራጀት፣

፮· ወደ ክምችቱ የሚገባውንና ከክምችቱ የሚወጣውን ምግብ ጥራት የመመርመርና የመቆጣጠር፣ የጥራት ደረጃውን ያልጠበቀ ምግብ እና ምግብ–ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች ወደ ክምችቱ እንዳይገቡ የማድረግ፣

፯· ምግብ–ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በብድርና በትውስት መልክ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ፣

፰· መጋዘኖችንና የማከማቻ አገልግሎቶችን የማሠራትና የማከራየት፣

፱· የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፣

፲· የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያግዙ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባሮችን የማከናወን።

፲· **የአስተዳደሩ አቋም**

አስተዳደሩ፦

፩· የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ)፣

፪· የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት የቴክኒክ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "የቴክኒክ ኮሚቴው" እየተባለ የሚጠራ)፣

፫· በኮሚሽነሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ሥራ አስኪያጅ፣

፬· አስፈላጊ ድርጅታዊ መዋቅርና ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።



6. *Ownership of the Reserve*

Ownership of the Reserve is vested in the Federal Government.

## PART THREE

## *Establishment of the Emergency Food Security Reserve Administration*

7. *Establishment*

1) Emergency Food Security Reserve Administration (hereinafter referred to as the "Administration") is hereby established under these Regulations.
2) The Administration shall be accountable to the Commission.

8. *Head Office*

The Administration shall have its head office in Addis Ababa and may establish ware houses and branch warehouse Administration offices in strategic locations which are found to be appropriate for Reserve holding.

9. *Powers and Duties of the Administration*

The Administration shall have the following powers and duties:

1) administer the Reserve;
2) obtain and receive the necessary food and non-food relief items for the Reserve from donations, purchase from domestic or external sources when deemed necessary;
3) store the food and non-food relief items obtained through donations or purchases;
4) release food from the reserve on loan to meet emergency food shortage as per the directives to be issued by the Emergency Food Security Reserve Board;
5) hold the necessary pesticides and chemicals required to prevent the food Reserve from pest attack, rotate grain stocks which stay in storage for a long period of time, and organize laboratory facilities on the food Reserve;
6) undertake quality control activities on the food which enters into the Reserve and released from the Reserve and prevent food and non-food relief items which do not meet their quality standards from entering into the Reserve;
7) avail non-food relief items for use, from the Reserve, in the form of loan or returnable basis as per the directive to be issued by the Emergency Food Security Reserve Board;
8) construct and rent warehouses and storage facilities;
9) own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name; and
10) perform other related activities to meet the objectives of the Administration.

10. *Organiazation of the Administration*

The Administration shall have:

1) An Emergency Food Security Reserve Board (hereinafter referred to as the "Board");
2) an Emergency Food Security Reserve Technical Committee (hereinafter referred to as the "Technical Committee");
3) a Manager to be appointed by the Government upon the recommendation of the Commissioner; and
4) the necessary organizational structure and manpower.

፬· ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አስቸኳይ የምግብ እጥረትን ለመቋቋም እንዲቻል ምግብ ከክምችቱ በብድር እንዲሰጥ መፍቀድ፤

፭· ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በድንገት የሚከሰቱ አደጋዎችን ለመቋቋም እንዲቻል ምግብ–ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች በብድር ወይም በትውስት መልክ ከክምችቱ ወጥቶ እንዲሰጥ መፍቀድ፤

፮· ምግብ–ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ክምችት አስተዳደር፣ አያያዝና አጠቃቀም በሚመለከት ለአስተዳደሩ ምክር መስጠት፣

፯· ምግብ–ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች ክምችቱን ዓይነት፣ መጠንና ደረጃ በሚመለከት በአስተዳደሩ በኩል ለቦርዱ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፤

፰· ምግብ–ነክ ያልሆነውን ክምችት አወጣጥ/አጠቃቀም/፣ ጥቅም ላይ የዋለውን ክምችት መልሶ ለመተካት የሚኖረውን ሥርዓት ለመዘርጋትና ለማሻሻል የሚረዱ ሀሳቦችን አጥንቶ በአስተዳደሩ በኩል ለቦርዱ ውሳኔ ማቅረብ፤ እና

፱· ሌሎች ቴክኒክ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ በራሱ አነሳሽነት ወይም ከአስተዳደሩ ጥያቄ ሲቀርብለት ምክር መስጠት።

፲፮· የቴክኒክ ኮሚቴው ስብሰባ

፩· የቴክኒክ ኮሚቴው ሰብሳቢው በሚያቀርበው ጥሪ መሠረት ይሰበሰባል።

፪· አስቸኳይ ስብሰባ ግን በሰብሳቢው ወይም ከግማሽ በላይ የኮሚቴው አባላት በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ሊጠራ ይችላል።

፫· ከቴክኒክ ኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ–ጉባኤ ይሆናል።

፬· የቴክኒክ ኮሚቴው ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ላይ በተገኙ አባላት ድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ድምጹ እኩል ከተከፈለ ግን ሰባሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

፲፯ የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

ሥራ አስኪያጁ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩· ሥራ አስኪያጁ የአስተዳደሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ፤ ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የአስተዳደሩን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፤

፪· በዚህ አንቀጽ፣ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ሥራ አስኪያጁ፣

ሀ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፱ የተመለከተውን የአስተዳደሩን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) አስተዳደሩን ያደራጃል፤ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግና ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ) እያንዳንዱ የበጀት ዓመት ከመጀመሩ ከሦስት ወር በፊት የአስተዳደሩን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ አቅርቦ በማስወሰን በኮሚሽኑ አማካኝነት ለመንግሥት ያቀርባል፤

መ) ለአስተዳደሩ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ዕቅድ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ተጠሪነታቸው ለራሱ የሆኑትን የአስተደደሩን የሥራ ኃላፊዎች በመምረጥ ለቦርዱ አቅርቦ ያሾማል፤

ረ) ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከክምችቱ ምግብ በብድር፣ ምግብ–ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶችን ደግሞ በብድር ወይም በትውስት ይሰጣል፤

4) decide the provision of food from the Reserve on loan to meet emergency food shortage as per the directive to be issued by the Board;

5) decide the provision of non-food relief items from the reserve on loan or returnable basis to withstand fast-onset-disasters as per the directive to be issued by the Board;

6) advise the Administration on issues related to the management, handling, and usage of the non-food relief items;

7) forward recommendations to the decision of the Board on the type, size, stock mix, and standards of non-food relief items Reserve, through the Administration;

8) study and forward recommendations to the decision of the Board to establish and improve procedures for the release/usage, and replenishment of non-food relief items released from the Reserve for use, through the Administration;

9) proivde advise to the Administration on other technical issues on its own initiative or when requested by the Administration.

16. *Meetings of the Technical Committee*

1) The Technical Committee shall be convened at the call of the chairman.
2) Extraordinary meeting may be convened at the call of the Manager or upon the request of more than half of the Technical Committee members.
3) There shall be a quorum where more than half of the members are present at a meeting of the Technical Committee.
4) Decisions of the Technical Committee shall be made by a majority vote, and in case of a tie, the chairman shall have a casting vote.

17. *Powers and duties of the Manager*

The Manager shall have the following powers and duties:

1) The Manager shall be the Chief executive of the Administration and shall, subject to the general directives of the Board, direct and administer the activities of the Administration.
2) Without limiting the generality stated under Sub-Article (1) of this Article, the Manager shall:
   (a) exercise the powers and duties of the Administration specified in Article 9 of these Regulations;
   (b) organize the administration, employ and administer employees of the Administration in accordance with the rules and regulations of the Federal Civil Service;
   (c) prepare the annual budget and work programme/plan of the Administration three months before the beginning of each budget year and submit, to the Government through the Commission upon the approval of the Board;
   (d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work plan of the Administration;
   (e) select officials directly responsible to him and forward them for appointment to the Board;
   (f) based on the directive to be issued by the Board, provide food on loan and non-food relief items on loan or returnable basis from the Reserve;

ለ) የቴክኒክ ኮሚቴውን እያማከረ በእያንዳንዱ ማከማቻ ቦታ የሚቀመጠውን የምግብ ክምችት መጠንና ስብጥር ያስፈጽማል፤

ሐ) በብድርና በትውስት የተሰጠው ምግብና ምግብ–ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች በወቅቱ መመለሳቸውን ይከታተላል፤

ሀ) አስተዳደሩ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ አስተዳደሩን ይወክላል፤

በ) ለአስተዳደሩ ሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለአስተዳደሩ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

፲፰· <u>የበጀት ምንጭ</u>

የአስተዳደሩ የበጀት ምንጭ፤

፩· መንግሥት ከሚመድብለት ዓመታዊ በጀት፤እና

፪· ከሌሎች ምንጮች ይሆናል።

፲፱· <u>ስለ ሂሣብ መዛግብት አያያዝና ስለ ምርመራ</u>

፩· አስተዳደሩ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብቶችን ከደጋፊ ሰነዶች ጋር በተሟላ መልኩ ይይዛል።

፪· የአስተዳደሩ የሂሣብ መዛግብትና የገንዘብ ነክ ጉዳዮች እንዲሁም የክምችቱ ሁኔታ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር ይመረመራል።

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፳· <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ ደንብ ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

፳፩· <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጳጉሜ ፩ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር



(g) upon the advice of the technical Committee, execute the maintenance of the grain quantity and mix that should be stored in each storage location;

(h) follow-up that the food and non-food relief items provided on loan or returnable basis from the Reserve are returned on time; and

(i) represent the Administration in all its dealings with third parties; and

(j) may delegate part of his powers and duties to the officials and employees of the Administration to the extent necessary for the efficient management of the Administration.

18. *Sources of Budget*

The Administration's budget shall be drawn from the following sources;

1) annual budget allocated by the government; and
2) from other sources:

19. *Books of accounts and Auditing*

1) The administration shall keep complete and accurate books of accounts with supporting documents.
2) The Administration's books of accounts and financial documents as well as the Reserve shall be audited at least once in a year by the Auditor General or by an auditor designated by him.

## *PART FOUR*
## *Miscellaneous Provisions*

20. *Inapplicable Regulations and Directives*

No Regulations and Directives inconsistent with these Regulations shall have effect with respect to matters provided for in these Regulations

21. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 6th day of September, 2000.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE